# ዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች

## የሁለተኛ ደረጃ መመረቂያ መስፈርቶች

*በዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ማረጋገጫ ዲፕሎማ የስርዓተ ትምህርት ይዘቱ ፣ የሚሰጠው ትምህርት ጥራት፣ እና የተማሪዎችን የመማር ብቃት በከፍተኛ ደረጃ ጠብቆ ለመሰጠቱ ማረጋገጫ ስለሆነ ተማሪው እና ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ዲስትሪክት በጋራ ተማሪው ለሥራ ዓለም ወይም ለከፍተኛ የትምህርት ተቋም ብቁ ሆኖ እንዲዘጋጅ ስለመደረጉ እንዲያስረዳ ተብሎ እንደተሰጠ የሰነድ ማስረጃ ተደርጎ መያዝ አለበት።*

---

**<u>አጠቃላይ ወይም ጥምር አጠቃላይ አስፈላጊ መወሰድ ያለባቸው ትምህርቶችና መስፈርቶች</u>**

ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው እንዲመረቁ እና ዲፕሎማ እንዲቀበሉ ሁለት መቶ አርባ የሴሚስተር ሰዓታት (24 ክፍሎች) ያስፈልጋሉ። ትራንስክሪፕቶች በመርሃግብር ይዘት መካከል ያለውን ልዩነት ማንጸባርቅ መቻል አለባቸው። ለጥምር አጠቃላይ ዲፕሎማ በማናቸውም የትምህርት መስክ በልዩ ትምህርት ኮርስ መርሃ ግብር ስር 140 የሴሚስተር ሰዓታት መማር ያስፈልጋል። የይዘት መስክ መስፈርቶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፥

| *የአጠቃላይ ትምህርት ኮርስ የዲፕሎማ መመረቂያ መስፈርቶች* | *ሴሚስተር* | *Carnegie* |
|---|---|---|
| **ኮርስ** | **ክሬዲትስ** | **ክፍሎች** |
| **1. የቋንቋ ስነ ጥበብ (Language Arts)** – ለስነ ጽሑፍ መግቢያ (Introduction to Literature) እና ስነ አጻጻፍ (Composition 1 & 2) አስር የሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል) እንዲሁም የአሜሪካ ስነ ጽሑፍ (American Literature 1 & 2) አስር ሰዓታት (1 ክፍል) ጨምሮ ቢያንስ አርባ የሴሚስተር ሰዓታት (4 ክፍሎች) መሸፈን አለባቸው። የዓለም ስነጽሑፍ (World Literature) ወይም የላይኛው ዲቪዝዮን የአጻጻፍ ኮርስ አስር የሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል)። በሌላ የቋንቋ ስነ ጥበብ ትምህርት አስር ሰዓታት (1 ክፍል)። | **40** | **4.0** |
| **2. ሒሳብ** – አርባ የሴሚስተር ሰዓታት (4 ክፍሎች) መሸፈን አለባቸው። አስር የሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል) ለ አልጄብራ ወይም እኩያው የአልጄብራ ኢንተግሬትድ ትምህርት፣ የጂኦሜትሪ አስር የሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል) ወይም እኩያው ኢንተግሬትድ ትምህርት፣ አስር የሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል) ለአልጄበራ ወይም እኩያው የአልጄብራ ኢንተግሬትድ ትምህርት፣ እና አስር የሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል) ከአልጄብራ ከፍ ያለ ትምህርት። | **40** | **4.0** |
| **3. ሳይንስ** – ሰላሳ ሴሚስተር ሰዓታት (3 ክፍሎች) መሸፈን አለባቸው፥ ተማሪዎች የሚከተሉትን ተምረው እንዲያጠናቁ ይገደዳሉ 30 ሴሚስተር ሰዓታት (3 ክፍሎች) የሳይንስ ክሬዲት፣ 20 ሴሚስተር (2 ክፍሎች) ከስነ መሬት (Earth) ሳይንስ፣ ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ ወይም ፊዚክስ ትምህርት የተገኘ መሆን አለበት። | **30** | **3.0** |
| **4. ማህበራዊ ጥናት (Social Studies)** – ሰላሳ ሴሚስተር ሰዓታት (3 ክፍሎች) መሸፈን አለባቸው። አስር የሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል) ለ የአሜሪካ ታሪክ፣ አምስት የሴሚስተር ሰዓታት (.5 ክፍል) በሲቪክስ፣ እና አስራ አምስት የሴሚስተር ሰዓታት (1.5 ክፍሎች) በሌሎች የማህበራዊ ጥናት ትምህርቶች። | **30** | **3.0** |
| **5. የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ዳንስ፣ ሲቲ ዋይድ ማርሽ ባንድ (Citywide Marching Band)፣ ROTC፣ ወይም DPS አትሌቲክስ** – አስር ሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል) መሸፈን አለበት ወይም ከአትሌቲክስ ተሳትፎ ለመውጣት ልዩ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። | **10** | **1.0** |
| **ኢሌክቲቭስ**– ሰላሳ ሴሚስተር ሰዓታት (9 ክፍሎች) መሸፈን አለባቸው<br>**አካዳሚክ ኢሌክቲቭስ** – አርባ ሴሚስተር ሰዓታት (4 ክፍሎች) ስነ ጥበብን፣ ዳንስን፣ ድራማን እና ሙዚቃን ወይም ሙያ እና ቴክኒክ ትምህርት ያካተተ የፋይን አርትስ ትምህርት ለ10 ሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል)። እንግሊዚዝኛ/ ማህበራዊ ጥናት ኢሌክቲቭስ፣ የዓለም ቋንቋ፣ AVID፣ Gear-Up እና AP/IB ኮርሶችን የሚያካትት የአካዳሚክ ኢሌክቲቭ ትምህርት ለአስር ሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል)።<br><br>**ሌሎች ኢሌክቲቮች** – ለመመረቅ ከሚያስፈልገው 240 ሴሚስተር ሰዓታት (24 ክፍሎች)፣ 50 ሴሚስተር ሰዓታት (5 ክፍሎች) ለኢሌክቲቮች መማር ይቻላል። በዋናዎቹ የስርዓተ ትምህርት የትምህርት ዓይነቶች ላይ ልዩ የተራዘመ የኢሌክቲቭ መርሃ ግብር ትምህርት ይሰጣል። በተጨማሪ፣ ተማሪዎች በስነ ጥበብ፣ በንግድ/ በገበያ ጥናት፣ የሸማች እና ቤተሰብ ጥናት፣ የውጭ ቋንቋ፣ ኢንዱስትሪያል ቴክኖሎጂ፣ ሙዚቃ፣ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ዳንስ፣ ወይም በልዩ ጥያቄ የሚሰጡ ትምህርቶች ኢሌክቲቮችን መምረጥ ይችላሉ።<br><br>**ማህበረሰብ ላይ የተመረኮዘ ተሞክሮ** – ለዲፕሎማ ከሚያስፈልገው 240 ሴሚስተር ሰዓታት (24 ክፍሎች)፣ ቢያንስ 220 ሴሚስተር ሰዓታት (22 ክፍሎች) በክፍል ውስጥ በሚሰጥ ትምህርት የተገኙ መሆን አለባቸው። ስለሆነም፣ ተማሪዎች ለመመረቅ እንደ መስፈርት ለማሟላት እንዲችሉ ግፋ ቢል ሃያ የሴሚስተር ሰዓታት (2 ክፍሎች) በማህበረሰብ ላይ የተመረኮዘ ተሞክሮ ትምህርት የሚቀስሙበትን መንገድ ማግኘት እና ተግባራዊ ልምምድ ማድረግ አለባቸው። እነዚህ ተሞክሮዎች የመስክ ወይም የአገልግሎት መስጠት ተሞክሮን፣ የሥራ ልምምድን እና የተመራቂ ሠራተኛ ልምምድ (ኢንተርንሺፕ) ሊያካትቱ ቢችሉም በነዚህ ብቻ የተገደቡ አይደሉም። | **90** | **9.0** |
| **ድምር** | **240** | **24.0** |

# የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የ2011 እና 2012 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መመረቂያ መስፈርቶች

**አጠቃላይ መረጃ**
**የሁለተኛ ደረጃ ውጤቶች በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ሊገኙ አይችሉም።** ለምሳሌ፦ አልጀብራ 1 በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያጠናቀቀ ተማሪ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገባ የግድ የአራት ዓመት የሒሳብ ትምህርት መማር አለበት።

**በልዩ ሁኔታ የሚታለፉ**
በዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቦርድ የታገዱ እና ከዚህ በታች የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ የአትሌትክስ ስፖርት ዓይነቶች ተማሪ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እንደ መመረቂያ መስፈርት እንዲማር እንዳይገደድ ሊያደርጉት ይችላሉ። ለአትሌቲክስ ተሳትፎ ምንም የትምህርት ውጤት ወይም ክሬዲት አያዝም እና እንዲህ መሰሎቹ መታለፎች ዲፕሎማ ለማግኘት ከሚያስፈልገው በትምህርት ላይ መዋል ካለበት ሰዓት ተቀናሽ ሆነው አይታሰቡም። ሁለቱም የግድ መወሰድ ያለባቸው የሁለት ሴሚስተር የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርቶች በአትሌቲክስ ተሳትፎ ሊካካሱ እና ሳይወሰዱ ሊታለፉ ይችላሉ።

**የሰውነት ማጎልመሻ ሳይማሩ ለመታለፍ የሚያስችሉ ገገር መስፈርቶች፥**

ሀ. ተማሪው ለመላው የትምህርት ዘመን አካዳሚያዊ ተገቢነቱን ማስጠበቅ መቻል አለበት።
ለ. አንድ ሙሉ በስፖርት ተሳትፎ የታለፈ የትምህርት ዘመን አንድን ተማሪ መውሰድ ካለበት የአካል ማጎልመሻ (PE) ትምህርት ግዴታ ነጻ ሊያደርገው ይችላል።
ሐ. ተማሪ በልዩ ሁኔታ መታለፍ እንዲችል የመጀመሪያ ዓመት፣ ሁለተኛ ዓመት ወይም ሶስተኛ ዓመት ተማሪ መሆን አለበት። መውሰድ ያለባቸውን የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ያልወሰዱ የአራተኛ ዓመት ተመራቂ ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ ሊታለፉ አይችሉም፣ ስለሆነም የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ለመማር መመዝገብ አለባቸው።

ከዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው ዲፕሎማ ተማሪው ከሚከተሉት አምስት የኮርስ ዓይነቶች ቢያንስ አንዱን እንዳሟላ ማረጋገጫ ይሰጣል፥

- አጠቃላዩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት
- እንዲማር የተመደበለት ኮርስ*
- ጥምር አጠቃላይ*
- የሥራ ልምምድ እና ትምህርት*
- ASCENT ዲፕሎማ (በተዛማጅ ምዝገባዎች የተማሪዎችን ትምህርት ማሳለጫ (Accelerating Students Through Concurrent Enrollment))

**ተጨማሪ መረጃ ስለመስፈርቶች**
በሒሳብ፣ እና በንባብ (Literacy CSAP) አጥጋቢ ውጤት ያላመጡ ወይም በክፊል ብቃት የሚጎድላቸው ተማሪዎች የ 9ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በሚማሩበት ዓመት፣ እና በአንዳንድ ሁኔታዎች የ 10ኛ ክፍል በሚማሩበት ዓመት እንዲደግሙ ይደረጋሉ። ይህ በድጋሚ የሚሰጥ ትምህርት እንደ አካዳሚክ ኢሌክቲቭ ክሬዲት ይቆጠራል።

በመደበኛው የትምህርት ዘመን አንድ ተማሪ 70 ክሬዲት ሰዓታት፣ (35 ክሬዲት በሴሚስተር) ማግኘት ይችላል። ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በሚሰጥ ልዩ ፈቃድ ገደቡ ወደ 80 ክሬዲት፣ (5 ተጨማሪ ክሬዲቶች በሴሚስተር) ከፍ ሊል ይችላል።

- አንድ ተማሪ በአንድ የክረምት ትምህርት ወቅት ሊወስድ የሚችለው ከፍተኛ የክሬዲት መጠን 10 የሴሚስተር ሰዓታት ብቻ ነው።

**የምረቃ ልምምድ**
በመመረቂያ ልምምዶች ላይ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ለመሳተፍ፣ ተማሪዎች በመመረቂያ ዓመታቸው ላይ የሚያስፈልገውን 240 ሴሚስተር ሰዓታት ማጠናቀቅ እና ሁሉንም ትምህርቶች ወስደው የጨረሱ መሆን አለባቸው።

**በሽግግር የመጡ ተማሪዎች**
ከዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውጭ በሽግግር የመጣ ተማሪ ከዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ዲፕሎማ ለመቀበል እንዲችል የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት። ሁሉም ለመመረቅ የሚያስፈልጉ መመዘኛ መስፈርቶች፣ በዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ቢያንስ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሳያቋርጡ መማር፣ እና ቢያንስ 50 የሴሚስተር ሰዓታት (5 ክፍሎች) ክሬዲት ማግኘትን ጨምሮ ከምረቃ በፊት መሟላት አለባቸው።

**በምረቃ ቀን ንግግር የሚያደርጉ ሁለት ምርጥ ተማሪዎች (Valedictorian/Salutatorian)**
በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በምረቃ ቀን ንግግር የሚያደርጉ አንደኛ እና ሁለተኛ የወጡ ተማሪዎችን ለመምረጥ የስምንቱ ሴሚስተሮች አማካኝ ጥቅም ላይ ይውላል። ተማሪዎች ንግግር ከሚያደርጉት ሁለት ምርጥ ተማሪዎች መካከል አንዳቸውን ለመሆን እንዲችሉ በትምህርት ቤታቸው ቢያንስ ለሶስት (3) ተከታታይ ዓመታት የተማሩ እና በመመረቂያ ዓመታቸው ላይ ያላቸው አጠቃላይ የአማካኝ ውጤት ከማንም የላቀ ከፍተኛ መሆን አለበት።

| የተማሪዎች የትምህርት ውጤት ደረጃ ምደባ | |
|---|---|
| 60 ሴሚስተር ሰዓታት | ሁለተኛ ዓመት |
| 120 ሴሚስተር ሰዓታት | ሶስተኛ ዓመት |
| 170 ሴሚስተር ሰዓታት | ተመራቂ |
| 240 ሴሚስተር ሰዓታት | ዲፕሎማ መስጠት |

# ዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች
## የሁለተኛ ደረጃ መመረቂያ መስፈርት የሥራ ልምምድ እና ትምህርት

*በዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ማረጋገጫ ዲፕሎማ የስርዓተ ትምህርት ይዘቱ፣ የሚሰጠው ትምህርት ጥራት፣ እና የተማሪዎችን የመማር ብቃት በከፍተኛ ደረጃ ጠብቆ ለመስጠቱ ማረጋገጫ ስለሆነ ተማሪዎቹ እና ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ዲስትሪክት በጋራ ተማሪዎች ለሥራ ዓለም ወይም ለከፍተኛ የትምህርት ተቋም ብቁ ሆኖ እንዲዘጋጁ ስለመደረጉ እንዲያስረዳ ተብሎ እንደተሰጠ የሰነድ ማስረጃ ተደርጎ መያዝ አለበት።*

---

**<u>የሥራ ልምምድ እና ትምህርት</u>**

ተማሪው ዕድሜው ሃያ አንድ ሲሆነው (21ኛ) ልደቱን ሲያከብር ባለው የመጀመሪያ ሴሚስተር በትምህርት ቤቱ ከተፈቀዱ እና በትምህርት ቤቱ ሠራተኞች የተመረጡለትን ትምህርቶች ለሁለት መቶ አርባ ሴሚስተር ሰዓታት (24 ክፍሎች) በ9ኛ፣ በ10ኛ፣ በ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ወስዶ ያጠናቀቀ መሆን መቻል አለበት። ትራንስክሪፕቶች በመርሃግብር ይዘት መካከል ያለውን ልዩነት ያንጸባርቃሉ። የይዘት መስክ እና የትምህርት መስፈርቶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፥

| ሥራ ልምምድ እና ትምህርት<br>የዲፕሎማ መስፈርቶች | የሴሚስተር ሰዓታት ያስፈልጋል | Carnegie ክፍሎች ያስፈልጋል |
|---|---|---|
| *ኮርስ* | *ክሬዲትስ* | *ክፍሎች* |
| **የሥራ ልምምድ እና ትምህርት መስፈርቶች (WES)** | | |
| **የቋንቋ ስነ ጥበብ**– ቢያንስ አርባ የሴሚስተር ሰዓታት (4 ክፍሎች) መወሰድ አለበት። | 30 | 3.0 |
| **ማህበራዊ ጥናት (Social Studies)** – ሃያ ሴሚስተር ሰዓታት (2 ክፍሎች) መሸፈን አለባቸው። አስር የሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል) በሙያ እና/ወይም በሽግግር ክፍሎች መውሰድ ያስፈልጋል። | 20 | 2.0 |
| **ሳይንስ** – አስር ሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል) መሸፈን አለባቸው፥ | 10 | 1.0 |
| **ሒሳብ** – ሃያ የሴሚስተር ሰዓታት (2 ክፍሎች) መሸፈን አለባቸው። | 20 | 2.0 |
| **የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ዳንስ፣ ሲቲ ዋይድ ማርሽ ባንድ (Citywide Marching Band)፣ ወይም ROTC** – አስር የሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል)<br>በ IEP በሌላ መልኩ ካልተገለጸ መሸፈን አለባቸው። | 10 | 1.0 |
| **ፋይን አርትስ፥ ሙዚቃ፣ ስነጥበብ፣ ድራማ ወይም CTE**– ስነጥበብ፣ ዳንስ፣ ድራማ እና ሙዚቃ ያካተተ የአስር ሰዓታት (1 ክፍል)። | 10 | 1.0 |
| **አካዳሚክ ኢሌክቲቭ** – የአካዳሚክ ኢሌክቲቭ አስር ሴሚስተር ሰዓታት (1 ክፍል) የሚከተሉትን ማለትም እንግሊዝኛ/ማህበራዊ ጥናት ኢሌክቲቭ፣ የሙያ እና ቴክኒክ ትምህርት ኮርሶች፣ AVID፣ Gear-Up፣ እና AP/IB ኮርሶች። | 10 | 1.0 |
| **ሙያ ትምህርቶች** – የሙያ ትምህርት አስር ሰዓታት (1 ክፍል) ያስፈልጋል። | 10 | 1.0 |
| **ሌሎች ኢሌክቲቮች፥** ለመመረቅ ከሚያስፈልገው 240 ሴሚስተር ሰዓታት (24 ክፍሎች)፣ 60 ሴሚስተር ሰዓታት (8 ክፍሎች) ለኢሌክቲቮች መማር ይቻላል። በዋናዎቹ የስርዓተ ትምህርት የትምህርት ዓይነቶች ላይ ልዩ የተራዘመ የኢሌክቲቭ መርሃ ግብር ትምህርት ይሰጣል። በተጨማሪ፣ ተማሪዎች በስነ ጥበብ፣ በንግድ/በገበያ ጥናት፣ የሸማች እና ቤተሰብ ጥናት፣ የውጭ ቋንቋ፣ ኢንዱስትሪያል ቴክኖሎጂ፣ ሙዚቃ፣ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ዳንስ፣ ወይም በልዩ ጥያቄ በልዩ ከትምህርት ጋር የተቀናጀ ሥራ ልምምድ የሚሰጡ ትምህርቶች ኢሌክቲቮችን መምረጥ ይችላሉ። | 60 | 6.0 |
| **በሥራ ላይ የተመረኮዘ ተሞክሮ** – ለዲፕሎማ ከሚያስፈልገው 240 ሴሚስተር ሰዓታት (24 ክፍሎች)፣ ቢያንስ 60 ሴሚስተር ሰዓታት (6 ክፍሎች) በሥራ ልምምድ በሚሰጥ ትምህርት (WES Program) የተገኙ መሆን አለባቸው። | 60 | 6.0 |
| **<u>እንዲማር የተመደበለት ኮርስ መስፈርቶች</u>**<br>እነዚህ መስፈርቶች የሚማረውን ትምህርቶች ዓይነት ይወስናሉ ወይም በትምህርት ቦርድ የጸደቀውን የስርዓተ ትምህርት/ይዘት የሚወክሉ መሆን አለባቸው። ዲፕሎማ ስለመስጠት ተገቢነት ውሳኔ በመስጠት ወቅት፣ የመገምገሚያ ስልቶች ይመረጡና ተማሪው የስሜት ሕዋሳት፣ የእጅ ወይም የመናገር ችሎታ ጉዳት ካለበት የሚደረገው ግምገማ የፈተናው ውጤት ትክክለኛውን የተማሪውን ችሎታ በሚገባ እንዲያንጸባርቅ እንጂ ተማሪው ያለበትን የስሜት ሕዋሳት፣ የእጅ ወይም የመናገር ችሎታ ጉዳትን የሚያንጸባርቅ መሆን የለበትም። | | |
| 1) የተቀመጡትን መስፈርቶች ለማሟላት እንዳይችሉ የሚያግዳቸው ከባድ ስር የሰደደ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ከላይ ከተጠቀሱት ኮርሶች የአንዱን መስፈርት ካሟሉ እና ለግል ብጁ ተደርጎ የተዘጋጀ ትምህርት የተቀመጠውን መስፈርት ካሟሉ በሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ሊመረቁ ይችላሉ።<br>2) ተማሪው ዕድሜው ሃያ አንድ ሲሆነው (21ኛ) የልደት በዓሉን ሲያከብር፣ በ IEP በሚወሰነው መሰረት በተከታታይ ሳያቋርጥ የ9ኛ፣ የ10ኛ፣ የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል አንደኛ ሴሚስተር ድረስ መማር አለበት። | | |
| **ድምር** | 240 | 24.0 |

*ጥምር አጠቃላዩ፣ እንዲማር የተመደበለት ትምህርት፣ እና የሥራ ልምምድእና ትምህርት አማራጮች የሚከተሉትን መስፈርቶች ለሚያሟሉ ተማሪዎች ብቻ ይሰጣሉ፥ ልዩ ትምህርት ስለጠና እንደሚያስፈልጋቸው የተወሰነላቸው ወይም አንድ ወይም ከዛ በላይ በሆነ ዋና የአካዳሚክ ወይም ኢሌክቲቭ ኮርስ ክሬዲት እንደ ልዩ ትምህርት የተቀመጠውን ክሬዲት ስለመውሰዳቸው ትራንስክሪፕታቸው የሚያሳይ ተማሪዎች። ለተማሪ የሚሰጠው ትምህርት በልዩ ሁኔታ በተዘጋጀ ዲፕሎማ ላይ ያልተንጸባረቀ ነገር ግን በተማሪው ትራንስክሪፕት ላይ የተለጸ ተማሪ። እያንዳንዱ የተማሪ ዲፕሎማ ፣ "ይህ ዲፕሎማ በኦፊሴሉ ትራንስክሪፕት ላይ የተመዘገበው ውጤት ግልባጭ ነው።" ማለት አለበት።

ተማሪው በሚከተለው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ቢያንስ አራት ዓመት (ስምንት ሴሚስተር) ሳያቋርጥ ከ9ኛ፣ 10ኛ፣ 11ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ መማር አለበት፥

- ሁሉንም የዋናውን የስርዓተ ትምህርት/ኢሌክቲቭ መስፈርት ያሟሉ 3.0 GPA ያላቸው ተማሪዎች እና 240 ሴሚስተር ሰዓታት (24 ክፍሎች) የተማሩ በሰባት ሴሚስተር ሊመረቁ ይችላሉ።
- ሁሉንም የዋናውን የስርዓተ ትምህርት/ኢሌክቲቭ መስፈርት ያሟሉ 3.5 GPA ያላቸው ተማሪዎች እና 240 ሴሚስተር ሰዓታት (24 ክፍሎች) የተማሩ በሰባት ሴሚስተር ሊመረቁ ይችላሉ።

**<u>የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች</u>**

የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን ዲፕሎማ ለማግኘት የሚከተሉትን ትምህርቶች መማር ይቻላል፥

- የአካል ጉዳት ያለባቸው *አጠቃላይ ትምህርት ኮርስ* መስፈርቶችን የሚያሟሉ ተማሪዎች *የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ዲፕሎማ ይቀበላሉ።*
- የአካል ጉዳት ያለባቸው *አጠቃላይ ትምህርት ኮርስ* መስፈርቶችን የሚያሟሉ ተማሪዎች *የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ዲፕሎማ ይቀበላሉ።*
- የአካል ጉዳት ያለባቸው *የሥራ ልምምድ እና ትምህርት መርሃግብር* መስፈርቶችን የሚያሟሉ ተማሪዎች *የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ዲፕሎማ ይቀበላሉ።*
- የተቀመጡትን መስፈርቶች ለማሟላት እንዳይችሉ የሚያግዳቸው ከባድ ስር የሰደደ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች እና ከላይ ከተጠቀሱት ኮርሶች የአንዱን መስፈርት ካሟሉ እና እንዲማሩ የተዘጋጀላቸውን ትምህርት መስፈርት ካሟሉ *የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ዲፕሎማ ሊቀበሉ ይችላሉ።*

መማር ስላለበት የትምህርት ዓይነት ለማወቅ የልጅዎን አማካሪ ወይም የልዩ ትምህርት መምህር ያነጋግሩ።

ተማሪው ያጠናቀቀው ኦፊሴል ትራንስክሪፕት ላይ የሚገለጽ ይሆናል።

**<u>የተሳትፎ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት</u>**

ትምህርታቸውን ሳያቋርጡ የተማሩ ነገር ግን በትምህርቱ የሚያስፈልገውን መስፈርት ከሶስቱ አንዱን የማያሟሉ ተማሪዎች የተሳትፎ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊሰጣቸው ይችላል።

**<u>አጠቃላይ መረጃ</u>**

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ለግል ብጁ የተደረጉ መርሃ ግብሮች ለተማሪዎች መዘጋጀት አለባቸው። የተማሪውን የትምህርት እና የሥራ ዓለም ግቦች መሳካትን በተመለከተ የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት፣ ተማሪ እና ወላጅ የጋራ ግዴታና ሃላፊነት ነው። **በራስ በግልጽ የተቀመጡ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ትምህርቶች** እያንዳንዱ ተማሪ በሶስተኛ የትምህርት ዓመቱ ላይ ሲደርስ በመጀመሪያው ሴሚስተር "በራሱ በግልጽ የሚቀመጡ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ትምህርቶችን" ያሳውቃል። ተማሪው ቢያንስ ከትምህርቱ 1.0 ክፍል ያክል ለመመረቅ ከሚያስፈልገው መስፈርት በላይ በአንድ የተወሰነ የይዘት መስክ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ አለበት (ሆኖም ግን ከሚያስፈልገው 240 የሴሚስተር ሰዓታት የግድ ማለፍ የለበትም)፣ እንዲሁም የአካዳሚያዊ ዕውቀቱን እና ምጥቀቱን የሚያሳይ የራሱ/የራሷ ትምህርት ደረጃ ማጎልበት አለበት/አለባት እንዲሁም ይህን ግንዛቤውን/ዋን ከሁለተኛ ደረጃ በላይም ተረድቶት ሊዘልቅበት ስለመቻሉ ማሳየት አለበት።

**የሁለተኛ ደረጃ ውጤቶች በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ሊገኙ አይችሉም።** ለምሳሌ፥ አልጄብራ 1 በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (MS) ያጠናቀቀ ተማሪ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገባ የግድ የአራት ዓመት የሒሳብ ትምህርት መማር አለበት።

**በልዩ ሁኔታ የሚታለፉ**

በዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቦርድ የታገዱ እና ከዚህ በታች የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ የአትሌትክስ ስፖርት ዓይነቶች ተማሪ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እንደ መመረቂያ መስፈርት እንዲማር እንዳይገደድ ሊያደርጉት ይችላሉ። ለአትሌቲክስ ተሳትፎ ምንም የትምህርት ውጤት ወይም ክሬዲት አያዝም እና እንዲህ መሰሎቹ መታለፎች ዲፕሎማ ለማግኘት ከሚያስፈልገው በትምህርት ላይ መዋል ካለበት ሰዓት ተቀናሽ ሆነው አይታሰቡም። ሁለቱም የግድ መወሰድ ያለባቸው የሁለት ሴሚስተር የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርቶች በአትሌቲክስ ተሳትፎ ሊካካሱ እና ሳይወሰዱ ሊታለፉ ይችላሉ።

**የሰውነት ማጎልመሻ ሳይማሩ ለመታለፍ የሚያስችሉ ገገር መስፈርቶች፥**

ሀ. ተማሪው ለመላው የትምህርት ዘመን አካዳሚያዊ ተገቢነቱን ማስጠበቅ መቻል አለበት።
ለ. አንድ ሙሉ በስፖርት ተሳትፎ የታለፈ የትምህርት ዘመን አንድን ተማሪ መውሰድ ካለበት የአካል ማጎልመሻ (PE) ትምህርት ግዴታ ነጻ ሊያደርገው ይችላል።
ሐ. ተማሪ በልዩ ሁኔታ መታለፍ እንዲችል የመጀመሪያ ዓመት፣ ሁለተኛ ዓመት ወይም ሶስተኛ ዓመት ተማሪ መሆን አለበት። መውሰድ ያለባቸውን የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ያልወሰዱ የአራተኛ ዓመት ተመራቂ ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ ሊታለፉ አይችሉም፣ ስለሆነም የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ለመማር መመዝገብ አለባቸው።